«ገቢው በየዓመቱ ለውጥ እያሳየነው»

- አቶ ተስፋዬ ቱሉ
በገቢዎች ሚኒስቴር የታክስ ሥርዓት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤ)

ገጽ 3



ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር አለመግባባት ቅሬታ በማቅረብ ሊፈታ ይችላል

ገጽ 4

Excise Tax




የገቢዎች ሚኒስቴር
Ministry of Revenues

# ገቢያችን ህልውናችን

አዳዲስ እና ትኩስ መረጃዎችን በነዚህ አድራሻዎች ይከታተሉ

ፌስቡክ:-
Ministry of revenues of Ethiopia
ዌብሳይት:-
www.mor.gov.et

12ኛ ዓመት | ቁጥር 146 | ታኅሣሥ 2014 ዓ.ም | በነፃ የሚታደል

## የስድስት ወር አፈጻጸሙ 92 በመቶ ተሳክቷል

የገቢዎች ሚኒስቴር የ2014 የመጀመሪያ ግማሽ በጀት ዓመት አፈጻጸም የዕቅዱ 92 በመቶ ተሳክቷል። ሚኒስቴር መ/ቤቱ በስድስት ወሩ ውስጥ ከታክስ እና ከጉምሩክ ቀረጥ ሊያስገባ ያቀደው 185 ቢሊየን 783.35 ሚሊየን ብር ሲሆን 171 ቢሊየን 310.38 ሚሊየኑን አሳክቷል።

አፈጻጸሙ ባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ላይ ተገኝቶ ከነበረው 149 ሚሊየን 97.76 ሚሊየን ብር የ22 ቢሊየን 212.62 ሚሊየን ወይም የ14.9 በመቶ ብልጫ አሳይቷል።

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለ2014 በጀት ዓመት ለማስገባት ያቀደው 360 ቢሊየን ብር ሲሆን የመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት አፈጻጸም ለዓመቱ ከተያዘው ዕቅድ የ47/59 በመቶ ድርሻ እንዳለው ከመ/ቤቱ ስትራቴጂክ ፕላንና ፕሮግራም አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የተገኘው መረጃ አመልክቷል።

## ግብር ከፋዮች እውቅና ተሰጣቸው

የአዳማ፣ የመካከለኛ እና የሐዋሳ ገቢዎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ግብር ከፋዮች እውቅና ተሰጣቸው። ግብር ከፋዮቹ እውቅና የተሰጣቸው በ2013 የግብር ዓመት የተሻለ የሕግ ተገዢነት ደረጃ በመሳየታቸው ነው።

ለግብር ከፋዮች የእውቅና ሰርተፊኬት ያበረከቱት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች፤ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አገልግሎት አሰጣጡን በማሻሻልና ውጤታማ አሠራሮችን በመከተል ለግብር ከፋዮች ምቹ ሁኔታን እየፈጠረ መሆኑን ተናግረው በገቢዎች ሚኒስቴር የተያዘውን እቅድ ለማሳካት ግብር ከፋዮችና አጋር አካላት የተቻለቸውን ርብርብ እንዲያደርጉ ጠይቀዋል።

የየቅ/ጽ/ቤቶቹ ሥራ አስኪያጆች በበኩላቸው፤ ታማኝ ግብር ከፋዮቹ አሁን ካሳዩት የሕግ ተገዢነት ባሻገር ታማኝ ያልሆኑት የሚያቀርቡትን የተጭበረበሩ መረጃዎችን ሀገርን ለከፋና ለውስብስብ ችግሮች ስለሚዳርጉ በመጠቆምም እንዲተባበሩ አሳስበዋል።

ግብር ከፋዮቹ ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል



የአዳማ ቅ/ጽ/ቤት



የመካከለኛ ቅ/ጽ/ቤት

## አቅመ - ደካሞች 102 ቤቶችን ተረከቡ

በራሔል ወልዴ

የገቢዎች ሚኒስቴር፣ የጉምሩክ ኮሚሽን እና ብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚገኙ ዜጎች ያስገነቧቸውን 102 ቤቶች ታኅሣሥ 27/2014 ዓ.ም. ለነዋሪዎች አስረከቡ።

በየካ፣ በቂርቆስ እና በቦሌ ክፍለ ከተሞች ለአቅመ-ደካሞች የተገነቡትን ቤቶች ያስረከቡት የገቢዎች ሚኒስትር አቶ ላቀ አያሌው እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወ/ሮ አዳነች አቤቤ ናቸው።

አቧሬ አካባቢ በተካሄደው የርክክብ ሥነ-ሥርዓት ላይ አቶ ላቀ አየሌው እንዳሉት፤ እንዲህ ዓየነት በጎ ተግባራት በቀጣይም እንዲከናወኑ ዜጎች የሚጠበቅባቸውን ቀርጥና ታክስ በወቅቱ መክፈል እና ደረሰኝን በአግባቡ መጠቀም አለባቸው።



አቧሬ ላይ ከተገነቡት ብበቶች መካከል፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወ/ሮ አዳነች አቤቤ በበኩላቸው፤ በበጎ ፈቃድ ሥራው ከሦስት ሺ በላይ ዜጎች ተጠቃሚ መሆናቸውን ተናግረዋል።



## ለእንግዶቹ ፈጣን አገልግሎት ተሰጥቷል

በሰለሞን ዘሪሁን

ከተለያዩ የዓለም ሀገራት ሀገራዊ ጥሪን ተቀብለው ወደ ኢትዮጵያ እየገቡ ላሉ መንገደኞች የጉምሩክ ኮሚሽን የተለየ የጉምሩክ አገልግሎት መስጫ ቦታ በማዘጋጀት ፈጣን አገልግሎት እየሰጠ ነው። በጉምሩክ ኮሚሽን የአዲስ አበባ ቦሌ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የመንደገኞች ጉዳይ ምክትል ሥራ አሥኪያጅ አቶ ዘራኤል ለአ እንደገለጹት፤ ለግልም ሆነ ለልገሳ ይዘዋቸው የሚመጡትን ዕቃዎች በአጭር ጊዜ እንዲረከቡ በትጋት እየተሠራ ነው።

በተለይ የህክምና ቁሳቁስ እና ሌሎች ድጋፎችን ይዘው የሚመጡ መንገደኞች ያመጧቸውን ዕቃዎች በቀላሉ እንዲስረክቡ ከጤና ሚኒስቴር እና ከሌሎች አጋር አካላት ጋር በመሆን መጋዘን ተዘጋጅቶ አገልግሎት እየተሰጠ እንደሰጠ ተናግረዋል።

ዲያስፖራዎቹን በተገቢው ሁኔታ ለማስተናገድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ በተቋቋሙ



ወደ ሀገር የገቡ ዳያስፖራዎች አየር መንገድ ላይ፤

የተለያዩ ኮሚቴዎች አማካኝነት ዝግጅት ስለተደረገ የ24 ሰዓት ፈጣን አገልግሎት መስጠቱን የገለፁት ደግሞ የቅ/ጽ/ቤቱ የዓለም አቀፍ መንገደኞች ቡድን አስተባባሪ አቶ ዝያድ ኑረታ ናቸው። እንግዶቹ ይዘው የመጡትን የተለያዩ ሀገራት ገንዘቦች በሕጋዊ መንገድ በመመንዘር ሀገራችን በቂ የውጭ ምንዛሬ እንድታገኝ በማድረግ ሀገር ወዳድነታቸውን እንዲያሳዩም አሳስበዋል።

ለእንግዶቹ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# ርዕሰ አንቀጽ

## ልምዳቸውን እንቅሰም

ሀገራችን ውስጥ በተከሰተው ጦርነት በተለይ የአማራ እና የአፋር ክልሎች በሽብርተኛ ኃይሎች በርካታ ቦታዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ የሰዎች እና የእንስሳት ሞት፣ ቁስለት፣ ስደት፣ የንብረት ውድመት እና ሌሎች የማኅበራዊ ቀውሶች ደርሰዋል። ይህን ሁሉ ኪሳራ ለመመለስ የተፋው ሕይወት መካሻ ባይገኝለትም የወደሙ ንብረቶች ሊተኩ ይገባል። ለዚህ ደግሞ መንግሥት፣ ኅብረተሰቡ እና ተቋማት በመረባረብ ላይ ቢሆኑም ከደረሰው ውድመት አኳያ አቅምን ተፈታታኝ ነው። ስለዚህ፤ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አህመድ አሳሳቢነት አንድ ሚሊየን ትውልደ-ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያውያን ከየሚኖሩባቸው የውጪ ሀገራት ወደሀገር ገብተው የቻሉትን ያህል እገዛ እንዲያደርጉ ጥሪ ተደርጓል። ይህንን ጥሪ በማክበር እና በመቀበል ወደተገመተው ቁጥር የሚጠጋ፤ በሒደትም ሊበልጥ የሚችል ጥሪው የሚመለከተው እንግዳ ይገባል።

በጥሪው መሠረት የገቡት ወገኖች ቀላል የማይባል የእርዳታ ዕቃን እያስገቡ ነው። ከዕቃዎቹ መካከል የመድኃኒት እና የትምህርት ቁሳቁሶች፣ አልባሳት፣ የንፅህና ዕቀዎች፣ ምግቦች፣ ወዘተ ተጠቃሾች ሲሆኑ እነርሱም ሆኑ ዕቃዎቹ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ መንገላታት እንዳይገጥማቸው በመንግሥት የተቋቋመ ግብረ-ኃይል በከፍተኛ ጥንቃቄ የተቀላጠፈ አገልግሎት እየሰጣቸው ነው።

እንግዶቹ በዓላትን አስታኮ የተጠሩበት ዋንኛ ዓላማ የተጎዳውን ህዝብ እንዲያግዙ ሲሆን ይዘዋቸው ከመጡት ዕቃዎች በተጨማሪ ገንዘቦቻቸውን በሕጋዊ መንገድ ሲመነዝሩ የውጪ ምንዛሪ አቅማችንን ያሳድጉታል። በተጨማሪም ደግሞ በሚያርፉባቸው ሆቴሎች፣ በሚጎበኟቸው የቱሪስት መስህቦች እና በሚጠቀሙባቸው አገልግሎቶች ቀላል የማይባል ገቢን ያስገኛሉ። ሌላው ደግሞ፤ ሀገራችን ውስጥ በመረጧቸው የኢንቨስትመንት መስኮች የሚሰማሩባቸውን ዕድሎች ያሰፋሉ። ከዚህ ባሻገር ደግሞ ከዘመድ ወዳጆቻቸው ጋር መልካም ጊዜን ያሳልፋሉ።

ዲያስፖራ እንግዶቻችን ዓለም አቀፍ ጫናን፤ በተለይም፣ ‹‹ወደ ኢትዮጵያ አትሂዱ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የምትገኙ የውጪ ዜጎችም ውጡ›› የሚለውን ማስፈራሪያ ባለማመን እና ከቁብም ሳይቆጥሩ በመምጣታቸው ነምግሥትን በማመናቸው ብቻ ሳይሆን ሳይጠራጠሩም ሆነ ሳይፈሩ በመምጣታቸው ጀግንነታቸውን ያሳያል።

እነዚህን እንግዶች በኢትዮጵያዊ የእንግዳ አቀባበል ልምዳችን መቀበል እንዳለብን ከማሳሰብ በተጨማሪ ግን የየመጡባቸውን ሀገራት መልካም ልምዶች መቅሰም አለብን። እንደሚታወቀው አብዛኞቹ የመጡት እና የሚመጡት በኢኮኖሚ አቅማቸው ካደጉት ሀገራት ነውና የሀገራቱ ልዩ ልዩ አሠራሮች የዘመኑ፤ የህዝባቸው አስተሳሰብም በዚያው ልክ የተራቀቀ ነው። ከዚህ ዕድገታቸው አንዱ የታክስ ተቋማቸው አሠራር እና የታክስ ከፋዮች የሕግ ተገዢነት ማደግ ነው። ይህን የመንግሥት አካላትም፣ ህዝብም አስበውበት ከፍተኛ የሆነ ልምድን ከመጠየቅ ጀምሮ በስብሰባም፣ በልዩ ልዩ ግንኙነቶችም መቅሰም ተገቢ ነው። መገናኛ ብዙኃንም በልዩ ልዩ የመረጃ መውሰጃ መንገዶቻቸው የዘመነ የታክስም ሆነ ሌላ አሠራራቸውን በመጠየቅ ለህዝብ ማድረስ፣ ሰንደው መያዝም ይጠበቅባቸዋል። ይህ ደግሞ እንግዶቹን ከተቀበሉ ቤተሰቦች ይጀምራልና ሁሉም ለበጎ ልምድ ቀሰማው ይትጋ።

ገቢያችን ህልውናችን፤ በገቢዎች ሚኒስቴር የኮምዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

የኤዲቶሪያል ቦርድ አባላት፡- ወ/ሮ ኡሚ አባጀማል ሰብሳቢ
አቶ እስክንድር መርሐጽድቅ አባል
አቶ ጋሻው ታደሰ አባል
አቶ ፀጥአርጋቸው ንጋቱ አባል
አቶ ዮሐንስ አዳሙ አባል

ዋና አዘጋጅ፡- እስክንድር መርሐጽድቅ
አዘጋጆች፡- ፀጥአርጋቸው ንጋቱ, ራሔል ወልዴ, በኃይሉ ሽመልስ, ሕይወት ገ/መድህን, ሰዒድ ገልገሉ, ሰለሞን ዘሪሁን

ጸሐፊና ሌይአውት ዲዛይነር፡- ብርሃኔ ደመቀ
ፎቶግራፈር፡- ክፍሌ አዳፍሬ፣ እስካለም ሰፊው እና የትናየት እንዳያፍሩ

አድራሻ፡- ስልክ 011-6-62-98-17 ፋክስ 011-6-67-39-14
ፖ.ሣ.ቁ 2559 ዌብሳይት www.mor.gov.et
ኢሜል ethioerca@Gmail.com
ፌስቡክ Ministry of revenues of Ethiopia

## ባለድርሻዎች ሕገ-ወጥነትን ስመከሳከል ሚናቸውን እንዲወጡ ተጠየቀ

**በሕይወት ገ/መድኅን**

የአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኮንትሮባንድና ህገ-ወጥ ንግድ እንቅስቃሴ በሀገር ላይ የሚያደርሰውን አደጋ ለመቀነስ የሚያስችል የምክክር መድረክ ከባለድርሻ አካላት ጋር አካሄደ። በምክክር መድረኩ ላይ ባለድርሻ አካላት ኮንትሮባንድን እና ሕገ-ወጥ ንግድን ለመከላከል በሚሠሩት ሥራዎች ላይ ተሳትፏቸውን እንዲያሳድጉ ጥያቄ ቀርቦላቸዋል።

ውይይቱን በንግግር የከፈቱት የአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ሥራ አሥኪያጅ አቶ ተፈሪ መኮንን፤ የሀገር ኢኮኖሚ በመጉዳት ፖለቲካዊና ማህበራዊ ቀውስ የሚፈጥረውን ኮንትሮባንድ ለመከላከል የሁላችንም እኩል ተሳትፎ ያስፈልጋል ብለዋል።

‹‹ኮንትሮባድን እከላከላለሁ፤ ሀገሬንም እታደጋለሁ!" በሚል መሪ ቃል በተካሄደው ውይይት፤ ባለድርሻ አካላትና ተገልጋዮች ይህንን የሀገር ህልውና አደጋ ለመግታት በሚደረገው ርብርብ የበኩላቸውን ድርሻ በመወጣት ሀገራዊ ኃላፊነታቸውን ጭምር እንዲወጡ ተጠይቀዋል። በዚህም መሠረት በድርጊቱ የሚሳተፉትን ከመከታተልና ከመቆጣጠር ጀምሮ በሚወሰደው እርምጃ ላይ ተሳትፏቸውን እንዲያበረክቱ ማሳሰቢያ ተሰጥቷቸዋል።

ቅ/ጽ/ቤቱ እየሠራቸው ባሉ የተለያዩ የአሠራር ለውጦች ኮንትሮባንድና ህገ-ወጥ የንግድ እንቅስቃሴን የመከላከልና የመቆጣጠር አቅም እያደገ መምጣቱን የቅ/ጽ/ቤቱ የሕግ ተገዥነት ዘርፍ ምክትል ሥራ አሥኪያጅ አቶ ስንታየሁ ረታ ገልጸዋል። እንዲሁም፤ እየተወሳሰበና እየረቀቀ በሚሄድ ላይ ያለውን ሕገ-ወጡን ተግባር ለማስወገድ የሠራተኞችን አቅም የመገንባት፣ በቴክኖሎጂ የታገዘ የመከላከልና መቆጣጠር ሥራን የመሥራት እና ቅንጅታዊ አሠራሮችን አጠናክሮ የማስቀጠል ተግባር እያደገ እንደሚሄድ ጠቁመዋል።

በውይይቱ ላይ የፌዴራል ምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ የጉምሩክ አስተላላፊዎች፣ የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት ኤጀንሲ፣ ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች፣ አስመጪዎች እና ላኪዎች ተገኝተዋል።

ከተሳፊዎቹ መካከል አንዳንዶቹ፤ ቅ/ጽ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀራርቦ በቅንጅት መሥራቱን ለቀልጣፋ አገልግሎት አሰጣጥ እንደሚያግዝ አመልክተዋል። እንዲሁም እንቅፋት የሚሆኑ አንዳንድ የአሠራር ክፍተቶችን በማረምና ዘመናዊ የአሠራር ሥርዓትን አጠናክሮ በማስቀጠል ኮንትሮባንድን እና ሕገ-ወጥ ንግድ መከላከል ላይ በአጭር ጊዜም ሆነ በሚፈለገው ልክ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ተናግረዋል።



በኮከብ አዳራሽ የተካሄደው የዋና መ/ቤት ሠራተኞች ውይይት፤



## በድኅረ-ጦርነት ስጋቶች ሳይ ውይይት ተካሄደ

የገቢዎች ሚኒስቴር አመራሮችና ሠራተኞች በድህረ ጦርነት እና ስጋቶች ላይ የሁለት ቀን ውይይት አድርገዋል።

ሀገራችን ያለችበት ወቅታዊ ሁኔታ ላይ ያተኮረው ውይይት መነሻ ያደረገው ወደፊት ስጋት የሚሆኑ ጉዳዮችን ለመከላከል መደረግ ስለሚገባቸው ነገሮች የታክስ ስርዓት ሚኒስቴር ዴኤታ አቶ ተስፋዬ ቱሉ ያቀረቡትን ማብራሪያ እና በንባብ የቀረበውን ሰነድ በመመርኮዝ ነው።

በማብራሪያው እና በሰነዱ ላይ የቀረቡትን ወቅታዊ ጉዳዮች አስመልክቶ ሠራተኞች አስተያየት ሰጥተው ጥያቄ ያቀረቡ ሲሆን በገቢዎች ሚኒስትር አቶ ላቀ አያሌው እና በሚኒስትር ዴኤታዎች ምላሽ እና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል።

ሚኒስትሩ፤ ከለውጡ በኋላ በሕውሓት ተበለሻሽተው የነበሩ ሀገራዊ ጉዳዮች ለሀገር በሚጠቅም መልኩ እየተስተካከሉ ቢሆንም አሁንም በቡድን፣ በጥቅም ትስስር፣ በሃይማኖት እና በዘር በመቧደን መጠቃቀም እና አገልግሎት መስጠት አልፎ አልፎ ስለሚስተዋል ሠራተኞች እና አመራሮች አገልግሎት አሰጣጣቸውን ከዚህ በጸዳ እንዳያደርጉት አሳስበዋል።

በገቢው ዘርፍ የተሰማራን አመራሮች እና ሠራተኞች ጦርነቱን ድል ለማድረግ ግንባር ከተሰለፈው ወታደር ባልተናነሰ አስተዋጽኦ አበርክተናል ብለው የእረፍት ጊዜን ጨምሮ በመሥራት በገቢው ዘርፍ ለተገኘው አመርቂ ውጤት ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

## ከ30 ሚሊየን ብር በሳይ የሚያወጣ እርዳታ ተሰጠ

**በጌታቸው ተሾመ**

የገቢዎች ሚኒስቴር እና ጉምሩክ ኮሚሽን 30.7 ሚሊየን ብር ዋጋ ያላቸው የተለያዩ እርዳታዎችን በሰሜን ወሎ በጦርነቱ ምክንያት ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉ እና ንብረታቸው ለወደመባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በእርዳታ ሰጡ። የተሰጡት እርዳታዎች ምግብ ነክ፣ ሽቀጣ ሸቀጥ፣ አልባሳት እና ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች ናቸው።

የህወሓት አሸባሪ ቡድን ወልዲያን ለአምስት ወራት ወ'ሮ በቆየባቸው ጊዜያት ህዝቡን በማረጋጋትና በማስተባበር እንዲሁም እርዳታ በማቅረብ የአባትነት ተግባራቸውን የተወጡትና በአሸባሪው ህወሓት ተሽከርካሪዎቻቸውን የተዘረፉት የሰሜን ወሎ እና ከሚሴ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ እና የቅዱስ ሲኖዶስ አባል ብፁዕ አቡነ ኤርሚያስ ከገቢዎች ሚኒስቴር፣ ከጉምሩክ ኮሚሽን፣ ከገንዘብ ሚኒስቴር እና ከትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር ስድስት ሚሊየን 76ሺ 665 ብር ወጪ የተደረገበትን ሎንግ ቤዝ ዘመናዊ ተሽከርካሪ በስጦታ ተበርክቶላቸዋል።

እርዳታውን እና ስጦታውን በሥፍራው ተገኝተው ያስረከቡት የገቢዎች ሚኒስትር አቶ ላቀ አያሌው፣ የጉምሩክ ኮሚሽነር አቶ ደበሌ ቃበታ፣ የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስትር ወ/ሮ ዳግማዊት ሞገስ እና የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ኢዮብ ተካልኝ ናቸው።

# እንግዳችን

አዘጋጅ፡- ራሄል ወልዴ

# «ገቢው በየዓመቱ ለውጥ እያሳየ ነው»

- አቶ ተስፋዬ ቱሉ
በገቢዎች ሚኒስቴር የታክስ ሥርዓት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤ)



**አገራዊውን ለውጥ ተከትሎ የገቢዎች ሚኒስቴር እንደገና ከተደራጀ ሦስት ዓመታትን አስቆጠረ። በለውጡ ምን ስራዎች ተከናወኑ? የተደረጉ ማሻሻያዎች ምንድን ናቸው? የገቢ እድገቱስ ምን ይመስላል? የሚሉና ሌሎች ጥያቄዎችን አንስተን በገቢዎች ሚኒስቴር የታክስ ስርዓት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ከሆኑት አቶ ተስፋዬ ቱሉ ጋር ቆይታ አድርገናል።**

**ባለፉት ሦስት የለውጥ ዓመታት ውስጥ በገቢው ዘርፍ የተሠሩ አንኳር ሥራዎች እና የተደረጉ ማሻሻያዎች ምንድን ናቸው?**

ለታክስ ስርዓቱ ማነቆ የነበሩ ችግሮችን ለመቅረፍ በርካታ ስራዎች በለውጡ ተሠርተዋል። ለአብነትም፤ በአደረጃጀት በኩል ከሰው ኃይል ስምሪት ጀምሮ የነበሩ ችግሮችን በመለየት ተጨማሪ ታክስ ማዕከላትን፣ የጉምሩክ ጣቢያዎችን እና ቅ/ጽ/ቤቶችን የመክፈት፤ የታክስ ኦዲት ተደራሽነትን ለማሳደግ ተጨማሪ የሰው ኃይል የመመደብ፤ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያን በተመለከተ ራሱን ችሎ በዳይሬክቶሬት ደረጃ የማደራጀት፤ በየቅ/ጽ/ቤቱ ተበትኖ የነበረውን የታክስ ኢንተለጀንስ ሥራዎች ከታክስ ስወራ ጋር ተያይዞ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በተጠናከረ ሁኔታ መርምሮ አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ እንዲያስችል በማዕከል የማደራጀት ሥራዎች ተሠርተዋል።

ሌላው፤ በሀገር ውስጥና በጉምሩክ አዋጆችና ደንቦች የሕግ ማዕቀፎች ላይ የነበሩ ክፍተቶችን የማሻሻል ሥራ ነው። በርካታ ክፍተት የነበረባቸው ለአፈጻጸም አመቺ ያልነበሩ የሕግ ማእቀፎች ማሻሻያ ተደርጎባቸዋል። በቴክኖሎጂ በኩል ለረዥም ጊዜ አገልግሎት ላይ የነበረውን ሲግታስ በአይታስ የመቀየር ሂደቶች ተጀምረዋል፤ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ላይ የነበሩ ችግሮችን በውስጥ አቅም የማሻሻል ሥራ ተሠርቷል። የኢ-ታክስ ስርዓትም ከለውጡ በኋላ ጥቅም ላይ የዋለ ቴክኖሎጂ ነው። የአግልግሎት ጥራትን በማሻሻል የሀብት ብክነትን በዚህ ስርዓት ማስቀረት ተችሏል። በአሁኑ ወቅት አብዛኞቹን አዲስ አበባ የሚገኙ ግብር ከፋዮች ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን በቀጣይ ሁሉንም ግብር ከፋዮች ወደ ሥርዓቱ የማስገባት ዕቅድ አለን።

**ማሻሻያዎቹ አሰራር ላይ ምን ለውጥ አምጥተዋል?**

ማሻሻያዎቹ በመደረጋቸው የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የነበሩ ችግሮች ተቀርፈዋል። ከለውጡ በፊት የነበረውን የተቋሙን ገጽታ መቀየር ተችሏል። በተከታታይ ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ ለሦስት ዓመታት የደንበኞች የእርካታ ደረጃ ላይ የተደረገ ጥናት እንደሚያሳው በየዓመቱ የደንበኞች እርካታ እየጨመረ ሄዷል። ከገቢ አንጻርም በየዓመቱ ለውጥ እየታየ ነው የመጣው። ለምሳሌ፡- ለውጡ በተጀመረበት በ2011 ዓ.ም 137 ቢሊየን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 120 ቢሊየን ብር መሰብሰብ ተችሏል። ይህ ከ2010 በጀት ዓመት አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር የ17 ቢሊየን ብር ብልጫ አለው። በ2012 በጀት ዓመት ደግሞ 156 ቢሊየን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 128.6 ቢሊየን ብር የተሰበሰበ ሲሆን ከ2011 በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸር የ8.4 ቢሊየን ብር ብልጫ አለው።

**በአመራርና በሠራተኛው ላይስ ያመጣው ለውጥ አለ?**

ከለውጡ በኋላ ሠራተኛው ላይ ከፍተኛ የሆነ የሥራ መነሳሳት በመፈጠሩ በእረፍት ቀናት ሳይቀር በሥራ ገበታው ላይ በመገኘት የገቢ እቅዱን ለማሳካት በቁርጠኝነት አገልግሎት እየሰጠ ነው።

አሁን ያለን አሠራር የቅ/ጽ/ቤቶችና የፈጻሚዎች የየቀን እቅድ ክትትል የሚደረግ በመሆኑ በየቀኑ የሚሰበሰበው ገቢ ሪፖርት የሚደረግ በመሆኑ ክፍተት ያለባቸውን ቦታዎች ድጋፍ የመስጠት ሥራ በዋናው መሥሪያ ቤት በኩል ይሠራል። ከለውጡ በፊት በርካታ ያልተመለሱ ጥያቄዎች በመኖራቸው ሠራተኛው ላይ አሁን የምናየው ተነሳሽነት አልነበረም።

**በፀጥታ ችግር ምክንያት የተፈጠረውን የገቢ ጉድለት ለማካካስ ምን እየተሠራ ነው?**

በሀገር ውስጥ ታክስ ከሐምሌ 2013 ዓ.ም. ጀምሮ ባሉት ወራት በነዚህ አካባቢ የሚገኙ ቅ/ጽ/ቤቶች ከእቅድ አንጻር ዘጠኝ ቢሊየን ብር ክፍተት አጋጥሟል። የገቢዎች ሚኒስቴር የጎደለውን ገቢ ለማካካስ የተለየ እቅድ አውጥቶ እየሠራ ነው። ሌላው፤ የታክስ ህግ ተገዢነት ላይ ከማስተማር ጀምሮ በተጠናከረ መልኩ በመሥራትና ቅስቀሳዎችን በማድረግ በራሳቸው አሳውቀው የሚከፍሉ ግብር ከፋዮች ቁጥር ለመጨመር እንዲሁም የኦዲት ጥራትና ተደራሽነትን በመጨመር ግብር ከፋዮችን በስጋት ደረጃቸው ለይተን የተፈጠረውን ጉድለት ለማካካስ እየሠራን ነው።

ግብር ከፋዮች አሁን አገሪቱ የገጠማትን የምንዛሬ እጥረት እና በወቅታዊ ጉዳይ በተፈጠረው ችግር የተፈጠረው የገንዘብ እጥረት እንዲቀረፍ ያለባቸውን የታክስ እዳ እንዲከፍሉ ሰፊ የቅስቀሳ ሥራዎች ይሠራሉ። የታክስ ስርዓትን ማዘመንና ከአጋር አካላት ጋር የሚሠሩ የቅንጅት ሥራዎችን በማጠናከር በ2014 ዓ.ም የግብር ዓመት ያቀድነውን እቅድ እናሳካለን የሚል እምነት አለኝ።

**በቀጣይ የሀገራችንን ወጭ በታክስ ገቢ ለመሸፈን ሚኒስቴር መ/ቤቱ የያዛቸው ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ምንድን ናቸው?**

የሀገራችን ኢኮኖሚ የሚያመነጨውን ገቢ በብቃት የመሰብሰብ አቅምን ለመጨመር የታክስ ጂዲፒ ምጣኔ በ2012 ዓ.ም 17 በመቶ ለመድረስ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም ማሳካት የተቻለው 10.5 በመቶ ነው። ይህ ከታቀደው አንጻር 6.7 በመቶ ክፍተት ሲኖረው ክፍቱን ካመጡት ምክንያቶች መካከል የታክስ ማጭበርበርና ሕገ-ወጥ ደረሰኞች መበራከት ተጠቃሾች ናቸው። በታክስ ላይ በሚፈጸሙ ወንጀሎች ምክንያት ወደ መንግሥት መግባት ያለበት ገቢ ወደ ግለሰቦች ካዝና እንዲገባ አድርጓል።

እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ የቴክኖሎጂ ማሻሻያዎችን ወደ ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ (e-invoice) ስርዓት የማድረስ ተግባራዊነት ያስፈልጋል። ተግባራዊ እስኪሆን ድረስም አሁን ያለው የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ በማዘመን ከደረሰኝ ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ለመቀነስ ይረዳል። ሌላው፤ በህቡዕ ኢኮኖሚ ውስጥ እየተንቀሳቀሱ ወደ ታክስ ስርዓቱ ያልገቡትን ታክስ ከፋዮች ወደ ታክስ መረቡ ማስገባት ይጠበቃል። ሥራው በገቢዎች ሚኒስቴር ብቻ መከናወን የማይችል በመሆኑ ሌሎች ተቋማት አጋር በመሆን ሊሰሩ ይገባል። በአጠቃላይ፤ የታክስ ህግ ተገዢነት ደረጃን በማሻሻል፣ የታክስ መሰረትን በማስፋትና የታክስ ምጣኔዎች ላይ ማሻሻያዎች በማድረግ አገራችን የምትፈልገውን ገቢ መጨመር እንችላለን።

**ያጋጠመውን የገቢ ክፍተት ለመሙላት ከግብር ከፋዮች ምን ይጠበቃል?**

ታክስን በጊዜው አሳውቆ መክፈል አላስፈላጊ ቅጣትና ወለድን የሚያስቀር በመሆኑ ወቅቱን ጠብቀው ሊከፍሉ ይገባል። እንዲሁም ሀገራችን አሁን ባለችበት ወቅታዊ ሁኔታና በውጭ ተጽእኖ ምክንያት የደረሰባትን የገቢ ክፍተት ለመድፈን ግብር ከፋዮች ለታክስ ሕጉ በመታመን እና ሕገ-ወጦችን በማጋለጥ የዜግነት ግዴታቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል።

# ለግንዛቤዎ

አዘጋጅ- አዝመራ መላኩ

# ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር አለመግባባት ቅሬታ በማቅረብ ሊፈታ ይችላል

### የግብር ከፋዩ መብትና ግዴታ

በሥራ ሂደት መብትና ግዴታን አውቆ መሥራት የመልካም ሥነ-ምግባር አንዱ መገለጫ ነው። በመልካም ሥነ-ምግባር የተገነቡ ሰዎች መብትና ግዴታቸውን በማወቅና በመተግበር ከማህበረሰቡ ጋር በጥሩ ግንኙነት በመኖር ከቤተሰባቸው አልፈው ለሀገራቸው ከፍተኛ አስተዋፆ ያበረክታሉ፤ በተቃራኒው በተግባር ላይ የማያውሉት ደግሞ አይደለም ለወገን ሊተርፉ ቀርቶ በራሳቸው ህይወት ላይም እንቅፋት ሲፈጥሩ ይስተዋላል። ግብር ከፋዮች ከገቢዎች ሚኒስቴር ጋር ባላቸው የሥራ ግንኙነት ያላቸው መብት እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### የግብር ከፋዮች/ተገልጋዮች መብት

- ተገልጋዮች በሥራ ላይ ስላሉ የግብር እና ቀረጥ ድንጋጌዎች፣ ተቋሙ ስለሚሰጣቸው አገልግሎቶችና ቅድመ ሁኔታዎች ተገቢውን መረጃ እንደ አግባብነቱ በስልክ፣ በድረ ገጽ እና በአካል በመቅረብ መረጃዎቹን የመጠየቅ፣ ምላሽ የማግኘት እና አገልግሎቶቹን የመጠቀም መብት አላቸው።
- ማንኛውም የተቋሙ ተገልጋይ በጾታ፣ በዘርና ቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃው እና መገለል አድልዎ ሳይደርስበት በተገቢው ሁኔታ አገልግሎት የማግኘት መብት አለው።
- ማንኛውም ተገልጋይ ክብሩና ስብዕናው ተጠብቆ የመስተናገድ እና ለሚያቀርባቸው አግባብነት ያላቸው የአገልግሎት ጥያቄዎች እንደሁኔታው አዎንታዊ ይሁን አሉታዊ ምላሽ የማግኘት መብት አለው።
- ተገልጋዮች ለሚያቀርቡት የአገልግሎት ጥያቄ ወዲያው ምላሽ ለመስጠት የማይቻልበት ሁኔታ ሲኖር እና ቀጠሮ የሚሰጣቸው ከሆነ በሂደት ላይ የሚገኘው ጉዳያቸው ምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ እንዲሁም የትና በየትኛው ክፍል እንደሚገኝ (ጉዳዩ እስኪጠናቀቅ በምስጥር መያዝ የሚገባቸውን ጉዳዮች ካልሆኑ በስተቀር) ጠይቀው የመረዳት መብት አላቸው።
- የተቋሙ ተገልጋዮች በተቋሙ አሠራር፣ በሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ሥነ ምግባር እና በአጠቃላይ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ቅሬታ ካላቸው ቅሬታቸውን የማቅረብ፣ ተገቢውን ወቅታዊ ምላሽ የማግኘትና የመደመጥ መብት አላቸው።
- በተቋሙ አገልግሎት አሰጣጥና አሠራር ዙሪያ የታዘቡትንና ቢሆን ይሻላል የሚሉትን ተገቢ አስተያየት በማመስገንም ሆነ በመተቸት በነፃነት የመግለጽ መብት አላቸው።
- አርአያነት ባለው ሁኔታ የግብር ግዴታቸውን የሚወጡ ግብር ከፋዮች ሽልማት የመቀበል መብት አላቸው።

### የግብር ከፋዮች/የተገልጋዮች ግዴታ

በፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ 983/2008 መሠረት ማንኛውም የታክስ ግዴታ የሚመለከተው ሰው/ ድርጅት:-

- በግብር ከፋይነት የመመዝገብ፣
- በሚኒስቴሩ የተፈቀደ ደረሰኝ የማሳተምና የመጠቀም፣
- ተገቢነት ያላቸው ሰነዶች የመያዝ፣
- ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ፣
- ግብይትን በደረሰኝ ብቻ የማከናወን፣
- በሕግ በተመለከተው ጊዜ ገቢውን ወይም ሽያጩን አሳውቆ ትክክለኛ ግብሩን/ታክሱን የመክፈል፣
- ከተከፋይ ሒሳብ ላይ ግብርን ቀንሶ የማስቀረትና ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ገቢ የማድረግ፣
- ሕጋዊና ትክክለኛ ደረሰኞችንና ሰነዶችን ብቻ የመጠቀም፣
- ለታክስ ተገቢነት ያላቸው ሰነዶችን በሕጉ ለተመለከተው ጊዜ ያህል ይዞ የመቆየት እንዲሁም
- በታክስ ደረሰኝና ሌሎች የግብይት ሰነዶች ላይ የገዥውን ወይም የአገልግሎት ተቀባዩን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የመፃፍ ግዴታዎች ተጥሎበታል።

ከነዚህ የታክስ አስተዳደር አዋጅ ግዴታዎች በተጨማሪ ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ግዴታዎች ተገልጋዮች ቢያውቋቸው መልካም ነው።

- ተገልጋዮች በታክስ ሕጎች የሚጠበቅባቸውን ግዴታ በታማኝነት የመወጣት፣ ስለግብር ጉዳዮች እውነተኛ መረጃ መያዝ እንዲሁም አስተያየት ሲሰጡም ሆነ ጥቆማና ቅሬታ ሲያቀርቡ ትክክለኛ መረጃ የመስጠት ግዴታ አለባቸው።
- ተገልጋዮች ማንኛውንም ከግብር ጋር የተያያዙ መረጃዎችን እንዲያቀርቡ ሲጠየቁ ትክክለኛ እና የተሟላ መረጃ በወቅቱ ማቅረብ ግዴታ አለባቸው።
- ማንኛውም ግብር ከፋይ የሚጠበቅበትን ግብር በተቀመጠው የሂሳብ ጊዜ ውስጥ በፈቃደኝነት የማሳወቅና የመክፈል ግዴታ አለበት።
- ግብር ከፋዮች ለታክስ ውሳኔ የሚያስፈልጉና በሕግ እንዲይዙ ግዴታ የተጣለባቸውን ሠነዶችና ማስረጃዎች በተደነገገው መሠረት በጥንቃቄ መዝግቦ መያዝ፣ ከአደጋና ስርቆት ጠብቆ በጥንቃቄ የማቆየት ግዴታ አለባቸው።
- ታክስ ከፋዮች በሚኒስቴር መ/ቤቱ ካስመዘገቡት የተለየ/የተጨማሪ የሥራ መስክ ላይ ሲሠማሩ፣ የአድራሻ ለውጥ ሲያደርጉ ወይም ሌላ የታክስ ከፋይነት አቋማቸው ላይ የተከሰተ ማናኛውም ለውጥ ሲኖር ለውጡን በሕግ በተደነገገው ጊዜ ገደብ ውስጥ ለተመዘገቡበት ገቢዎች መ/ቤት የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው።
- ተገልጋዮች ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ማግኘት የሚችሉትንና የሚገባቸውን አገልግሎት ሲጠይቁ አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታ ማሟላት፣ ከብልሹ ሥነ ምግባር በፀዳ እና የሚኒስቴር መ/ቤቱን የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች መብት በማይጋፋ ሕጋዊ አግባብ ጥያቄያቸውን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።

የግብር ወይም የታክስ ግዴታን ያለመወጣት የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩም ከግብር ሕጉ ጋር አለመተዋወቅም አንዱ ነው። የግብር ሕጉን አውቆ ችላ በማለትም ሆነ ባለማወቅ የግብር ግዴታን አለመወጣት ለተለያዩ አስተዳደራዊ ወይም የወንጀል ክስና ቅጣት ይዳርጋል። ማንም ሰው በንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ ለመግባት ሲፈልግም ሆነ ገብቶ ሲገኝ የሀገሪቱን የግብር እና የንግድ ሕጎች ካልሆነም የተሠማራበትን የንግድ ዘርፍ የሚመለከቱትን ሕጋዊ ግዴታዎችና መብቶችን ማወቅ ብልህነት ነው።

በታክስ ውሳኔ አለመግባባት ሲፈጠር በየደረጃው አቤቱታ የሚቀርብበት የተቋሙ ሂደት አለ። ከዚህም ውስጥ የታክስ ቅሬታ አንዱ ነው።

### በታክስ ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ የቅሬታ ማስታወቂያ

በታክስውሳኔ ቅር የተሰኘ ታክስ ከፋይ የውሳኔውንማስታወቂያ በደረሰው በ21 ቀናት ውስጥ በውሳኔው ላይ የቅሬታ ማስታወቂያ ለባለሥልጣኑ በጹሑፍ ማቅረብ ይችላል።

ቅሬታ የቀረበበት የታክስ ውሳኔ በተሻሻለ የታክስ ስሌት ላይ ከሆነ የታክስ ከፋዩ ውሳኔ በተሻሻለ የታክስ ስሌት የመቃወም መብት የመጀመሪያ ውሳኔ የታክስ የመቃወምመብት የመጀመሪያውን የታክስ ስሌት የመቃወም መብት የመጀመሪያውን የታክስ ስሌት በመለወጥ፣በመቀነስ ወይም በመጨመር በተደረገው ማሻሻያ ላይ ብቻ የተገደበ ይሆናል።

በታክስ ከፋይ የቀረበ የቅሬታ ማስታወቂያ በአግባቡ እንደቀረበ የሚቆጣጠረው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ነው።

- የቅሬታ ማስታወቂያው ታክስ ከፋዩ የታክስ ውሳኔውን ለማስተካከል ሊደረጉ ይገባል ብሎ የሚያምንባቸው ማሻሻያዎች እና እነዚህን ማሻሻያዎች ማድረግ አስፈላጊ የሆነበትን ምክንያቶች በትክክል የሚገልጽ ከሆነ፣
- ቅሬታው ከታክስ ስሌት ጋር የተገናኘ ከሆነ ታክስ ከፋዩ በታክስ ስሌት መሠረት መክፈል ያለበትን እና በቅሬታ ማስታወቂያው ተቃውሞ ያላቀረበበትን ታክስ የከፈለ እንደሆነ እንዲሁም
- በታክስ ውሳኔው ላይ ቅሬታ ቢኖረውም ታክሱን ከፍሎ የቅሬታ ማስታወቂያ ማቅረብን የመረጠ ከሆነ የተወሰነበት ታክስ ከከፈለ ነው።

ባለሥልጣኑየቅሬታ ማስታወቂያው በአግባቡ አልቀረበም ብሎ ሲያምን ለታክስ ከፋዩ የሚከተሉትን የሚገልጽ የጹሑፍ ማስታወቂያ ወዲያውኑ ይሰጠዋል:-

ሀ. ቅሬታው በአግባቡ አልቀረበም የሚልባቸው ምክንያቶች እና

ለ. ከሚከተሉት በዘገየው ጊዜ ውስጥ ታክስ ከፋዩ ቅሬታውን ካላቀረበ የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜ ውስጥ ታክስ ከፋዩ ቅሬታውን ካላቀረበ የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜ እንደሚያልፍ፣

- ቅሬታው የሚመለከተው የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ21 ቀናት ውስጥ ወይም

* ህግ መሠረት የሚሰጠው ማስታወቂያ በደረሰው በ10 ቀናት ውስጥ።

የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈ ከሆነ ባለሥልጣኑ ይህንን የሚገልጽ የጹሑፍ ማስታወቂያ ለሚመለከተው ታክስ ከፋዩ ይሰጣል። ማመልከቻ ሲቀርብ፣ባለሥልጣኑ:-

ሀ. ታክስ ከፋዩ በኢትዮጵያ ውስጥ ያልነበረ በመሆኑ በህመም ምክንያት ወይም በሌላ አጥጋቢ ምክንያት በተወሰነው ጊዜ ውስጥ የቅሬታ ማስታወቂያውን ማቅረብ አለመቻሉ እና

ለ. የቅሬታ ማስታወቂያውን ለማቅረብ በታክስ ከፋዩ በኩል ምክንያታዊ ያልሆነ መዘግየት አለመኖሩ ሲያምንበት የተመለከተው የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜው ካበቃበት ቀን ጀምሮ ከ10 ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ሊያራዝም ይችላል።

የታክስ የቅሬታ ማመልከቻ ይዘት

በታክስ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ታክስ ከፋይ ቅሬታውን ሲያቀርብ የሚከተሉትን ያሟላ መሆን አለበት:-

I. ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበው የቅሬታ ማስታወቂያ የቅሬታውን ፍሬ ነገር ምክንያቶች መያዝ አለበት፤

II. ከላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ቅሬታ አቅራቢው:-

- የቅሬታ አቅራቢውን ስም፣ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር እና አድርሻ፣
- ቅሬታ የቀረበበትን የታክስ ውሳኔ ይዘት፣
- ውሳኔውየተሰጠበትንቀን፣
- ውሳኔየሰጠውንቅ/ጽ/ቤትእና
- ሌሎች ለውሳኔ የሚረዱ ፍሬ ነገሮችና ማስረጃዎችን መግለጽ አለበት።

III. ቅሬታ አቅራቢው የንግድ ፈቃድ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የምስክር ወረቀት፣ እንዲሁም ጉዳዩ በታክስ ወኪሉ የሚቀርብ ከሆነ ለወኪሉ ቅሬታ አቅራቢው ውክልና የሰጠበት ማስረጃ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ከሆነ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማቅረብ አለበት፤

IV. የቀረበውን ቅሬታ የሚያስረዳ አግባብ ያላቸው ሌሎች ኮፒ የሰነድ ማስረጃዎች ከዋናው ጋር እንዲገናዘቡ ከቅሬታ ማመልከቻው ጋር በአባሪነት ማቅረብ ይኖርበታል።

V. የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አቅራቢው የሚያቀርበው ቅሬታ ባልተስማማበት የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ላይ እንጅ በተስማማበት የታክስ ስሌት ላይ ስላልሆነ በታመነበት ላይ መክፈል ካለበት ሊከፈል ይገባል።

### የታክስ ውሳኔ ቅሬታ ማመልከቻ የሚቀርብበት ቀንና አቀራረብ

- የቅሬታ ማመልከቻው በቅሬታ አቅራቢው ወይም በሚወክለው የታክስ ወኪል ተፈርሞ የገቢ ማህተም ተደርጎበት ለታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ሪከርድ ሥራ አመራር ባለሙያ መቅረብ አለበት።
- የቅሬታ ማመልከቻው በቅሬታ አቅራቢው እንደቀረበ የሚቆጠረው የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የገቢ ማህተም በተደረገበት ቀን ነው።
- የቅሬታላይ ውሳኔ የሚሰጥበት የጊዜ ገደብ
- በታክስ ውሳኔ ላይ ታክስ ከፋዩ ላቀረበው ቅሬታ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ቅሬታው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት አንድ መቶ ሰማንያ ቀናት ውስጥ ለቅሬታው ውሳኔ መስጠት አለበት፤
- በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ቅሬታ አጣሪው ውሳኔ ካልሰጠ ቅሬታ አቅራቢው የአንድ መቶ ሰማንያ ቀናት ጊዜ ገደብ ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት በ30 ቀናት ውስጥ ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ይግባኝ ማቅረብ ይችላል።
- በቀረቡ ቅሬታዎች ላይ ጽ/ቤቱ ለተጨማሪ የማጣራትሥራ ውሳኔውን ለወሰነው የሥራ ክፍል የሚሰጠው ጊዜ ከአንድ ወር መብለጥ የለበትም።
- በቅሬታ ላይ ውሳኔ ስለመስጠት
- በአግባቡ የቀረቡ ቅሬታዎችን በነጻነት በመመርመር በቅሬታዎቹ ላይ ለሚሰጠው ውሳኔ የውሳኔ ሀሳብ የሚቀርብ ቋሚ የሥራ ክፍል ያቋቁማል።
- የሥራ ክፍሉ በታክስ ስሌት ላይ የቀረበውን ቅሬታ ሲመረምር በታክስ ስሌቱ የተመለከተው በታክስ መጠን ሊጨምር ይገባል የሚል እምነት ሲኖረው፣የሥራ ክፍሉ የታክስ ስሌቱ ለሚመለከተው የታክስ ሠራተኛ ተመልሶ እንደገና እንዲታይ የውሳኔ ሃሳብ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይኖርበታል።
- ባለሥልጣኑ በሥራ ክፍሉ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ከመረመረ በኋላ የቀረበውን ቅሬታ በሙሉ ወይም በከፊል በመቀበል ወይም ውድቅ በማድግ ውሳኔ የሚሰጥ ሲሆን ውሳኔውም "በቅሬታ ላይ የተሰጠ ውሳኔ" ተብሎ ይጠቀሳል።
- ባለሥልጣኑ በቅሬታ ላይ የሰጠውን ውሳኔ ለታክስ ከፋዩ በጹሑፍ የሚያሳውቀው ሲሆን በታክስ ስሌት ላይ የቀረበ ቅሬታ ከሆነ የታክስ ስሌቱን ማሻሻል ጨምሮ ውሳኔውን ለማስፈፀም አስፈለጊ የሆኑትን እርምጃዎች ይወሰዳል።
- ቅሬታ ላይ የተሰጠ ውሳኔ ማስታወቂያ የጉዳዩን ዋና ፍሬ ነገሮች፣ ግኝቶች እና በውሳኔ መሠረት የሆኑትን ምክንያቶች እና ለኮሚሽኑ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚቻል የሚገልጽ መግለጫ ማካተት አለበት።




# በየዓይነቱ

አዘጋጅ፡- በኃይሉ ሺመልስ



## የናቁት መዳኛ

በመሰንበት አድማሱ



ድፍን ኬንያዊያንን በእንባ ያራጨው ምስኪን የጓዳና ተዳዳሪ ጆን የእለት ጉርሱን ለምኖ በረንዳ የሚያድር ህጻን ሲሆን ትራፊክ መብራት ላይ መኪኖች ሲቆሙ በመስኮት ሄዶ ይለምናል። አንድ ቀን እንደተለመደው ወደ አንድ መኪና ተጠግቶ በመስኮት እጁን ሲዘረጋ በተከፈተው የመኪናዋ መስኮት ግላዲ ካማዳ ከተባለች ሴት ጋር ፊት ለፊት ይተያያል። ልመናውን ትቶም አንገቷ ላይ ስላለው ምንነት ይጠይቃታል። እሷም ጎዳና ተዳዳሪ በመሆኑ እና በመቆሸሹ ሳትንቀው በሰው ሰራሽ መተንፈሻ አክስጅን የምትተነፍስ፣ በእግሯ መንቀሳቀስ የማትችል እና መታከሚያ ገንዘብ ስለሌላት ሰባት ዓመት ሙሉ በዚህ በሽታ የምትሰቃይ መሆኗን ትነግረዋለች።

በሰማው እና ባየው ነገር ያዘነው ጆን እንባውን መቆጣጠር አቅቶት ልመናውን በማቋረጥ በልመና የሰበሰባትን ጥቂት ገንዘብ በሙሉ ታከሚበት ብሎ ይሰጣታል። እንባውና ሁኔታው የገረማቸው መንገደኞችም ተደንቀው የልጁን የሃዘን ገጽታ የሚያሳይ ምስል በፎቶ ካሜራቸው አንስተው በመገናኛ ብዙኃን ይለቁታል። ከዚያም በርካታ ኬንያውያን ምስሉን ተቀባበለው፣ ‹‹ይሄ ህጻን ምንም ሳይኖረው የዳቦ መግዣውን ከሰጠ እኛስ?›› ብለው ለህክምና የተጠየቀችውን አራት ሚሊዮን ሽልንግ አሰባሰቡላት።

ግላዲ ዛሬ በዚህ የጎዳና ተዳዳሪ ህጻን መነሻነት ባገኘችው ገንዘብ ወደ ህንድ ሀገር ተጉዛ ስለታከመች አክስጅኗን ጥላ በነጻነት እየተነፈሰች ሙሉ ጤነኛ ሆናለች፤ ሥራዋንም በተገቢው ውኔታ እያከናወነች ትገኛለች።

ለመስጠት የግድ ሃብታም መሆን አይጠበቅብንም። ማንም ሰው ‹‹ልስጥ›› ካለ የሚሰጠው አያጣም። ፈጣሪ ሊረዳህ ከፈልገ አንተ ባልጠበቀው እና አንተ በናቅኸው ሰው ባልገመትከው መንገድ መጥቶ ይረዳሃል። ይህች ሴት ‹‹የጎዳና ተዳዳሪ ነው›› ብላ ንቃው የመኪና መስኮቷን ዘግታ ቢሆን ኖሮ ዛሬ ለዚህ ዘእድል ባልበቃች ነበር። በተናቀው እና በቆሸሸው ሰው ውስጥ ፈጣሪ ለብዙዎቻችን የሚሆን ምላሽ እና ትንሽ በሚመስል ነገር ትልቅ ዓላማ አለውና ማንንም ሰው አንናቅ።

## ስጦታ

አንዲት ወጣት ዓይነ-ስውር በመሆኗ ሕይወቷን አምርራ ትጠላ ነበር። ነገር ግን በልቧ የምትፈቅደውና የምትወደው አንድ የወንድ ጓደኛ ነበራት። ባላት ፍቅር ምክንያት ዓይኗ ድኖ ማየት ብትችል እንደምታገባው ትናገር ነበረ።

አንድ ቀን አንድ ሰው ዓይኖቹን በስጦታ አበረከተላትና ሁሉንም ነገር ማለትም ፍቅረኛዋንም ጭምር ማየት ቻለች። ጓደኛዋም፣ “ታገቢኛለሽ?” ሲል ጠየቃት። ልጅቱ ግን ጓደኛዋ ዓይነ-ስውር መሆኑ ስታይ ደነገጠች። እናም የጋብቻ ጥያቄውን ውድቅ አደረገች። ይኼኔ ያ ምስኪን አፍቃሪ በእንባ እየታጠበ ጽፎ የላከላት ማስታወሻ፣ “ውዴ አደራ፤ ዓይኖቼን በጥንቃቄ ተንከባክበሽ ያዠቸው” የሚል ነበር።

እንግዲህ የሰው ልጅ አዕምሮ እንደዚህ ነው። ከሁኔታወች መለዋወጥ ጋር አብሮ የሚለዋውጠው ይበዛል። ጥቂቶች ብቻ ናቸው ትናንትን ዘወር ብለው የሚያዩት።

ሰውን ሁለት ነገር ይገልፁታል። የመጀመሪያው ምንም የሌለው ጊዜ የሚያሳየው ትዕግስት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሁሉም ሲሟላለት የሚያሳየው ጠባይ ነው። ስለዚህ፤ መጥፎ ነገር ከመናገር በፊት መናገር የማይችሉ እንዳሉ፣ ስለ ምግብህ ጣዕም ከማማረርህ በፊት የሚቀምሱት የሌላቸውን፣ ስለ ትዳር ጓደኛህ ከማማረርህ በፊት ውሃ አጣጪ የሌለውን፣

ስለ ኑሮ ከማማረርህ በፊት በልጅነት የተቀጨውን ማሰብ ተገቢ ነው። ቆም ብለህ በማሰብ ዛሬ የምታማርርበትን ህይወት ሌሎች ያጡትና የሚመኙት መሆንን ማስታወስ ይገባል። ትናንትንም ዘወር ብሎ በመቃኘት ለዛሬ መሠረት መሆኑን በመገንዘብ ክብር መስጠት ያስፈልጋል።

**ምንጭ**:- ደሊበርድ ኤክስትራን



## ኮሚሽኑ ለመቄዶኒያ ድጋፍ አደረገ

የጉምሩክ ኮሚሽን ለመቄዶኒያ የአረጋውያንና የአእምሮ ህሙማን መርጃ ማእከል የተለያዩ ቁሳቁሶችን በመለገስ በማዕከሉ ለሚረዱ አረጋውያንና አእምሮ ህሙማን የምሳ ግብዣ አደረገ::

ግምታቸው 27.4 ሚሊየን ብር የሆነውን አልባሳት፣ ምግብነክ፣ የማብሰያ እቃዎችና የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች እርዳታ ለማዕከሉ መስራችና ሥራ አሥኪያጅ ለአቶ ቢኒያም በለጠ ያስረከቡት የጉምሩክ ኮሚሽነር ደበሌ ቃበታ ናቸው::

ከ40 ተረጂዎች ተነስቶ አሁን ከ7000 በላይ ወገኖችን በማገዝ ላይ ለሚገኘው ለዚህ ማዕከል ኮሚሽኑ እስካሁን ከ102 ሚሊየን ብር በላይ የሚያወጡ ቁሳቁሶችን ድጋፍአ ድርጓል::

## ጦርነቱ በተካሄደባቸው አካባቢዎች ከ2.3 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ አልተሰበሰበም

የትግራይ ወራሪ ኃይል በከፈተው ጦርነት ትግራይን ጨምሮ በወረራ ተይዘው በነበሩት አካባቢዎች ሊሰበሰብ የነበረው ከ2.3 ቢሊየን በላይ ብር እንዳልተሰበሰበ የገቢዎች ሚኒስቴር የኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር ወ/ሮ ዑሚ አባጀማል አስታወቁ። ከነዚህ ውስጥ ከመቀሌ ገቢዎች ሚኒስቴር እና ጉምሩክ ኮሚሽን ቅርንጫፎች ጽ/ቤቶች ሊሰበሰብ ከታቀደው 1.8 ቢሊየን ብር ምንም ገቢ እንዳልተሰበሰበ አመልክተዋል።

በተመሳሳይ በኮምቦልቻ ገቢዎች ሚኒስቴር እና ጉምሩክ ኮሚሽን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችም 2.3 ቢሊየን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 1.9 ቢሊየን ብር ብቻ እንደተሰበሰበ ተናግረዋል። ከሁለቱም ቅርንጫፎች ይሰበሰባል ተብሎ የታቀደው 3.3 ቢሊየን ብር ቢሆንም የተሰበሰበው 1.9 ቢሊየን ብር ብቻ በመሆኑ ቀሪው 2.3 ቢሊየን ብር ሳይሰበሰብ መቅረቱን ገልጸዋል።

ጦርነቱ በአገር ኢኮኖሚ ላይ ያደረሰው ጫና በገቢው ላይ ብቻ ሳይሆን በበርካታ ዕቃዎችና ጽ/ቤቶችም ላይ መከሰቱን አመልክተው ኮምቦልቻ የሚገኙት የገቢዎች እና የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከነቁሳቁሳቸው ሙሉ በሙሉ እንደወደሙ ጠቁመዋል። በቀጣይም የተጎዱት እና ሌሎቹም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተረባርበው የተመዘገበውን የገቢ ክፍተት እንደሚሞሉት ወ/ሮ ዑሚ አስታውቀዋል።

## ግብር ከፋዮች እውቅና...

ከገጽ 1 የዞረ




ታማኝ ግብር ከፋዮቹ በበኩላቸው

ዕውቅና የተሰጣቸው ባሟሉት መሰረታዊ የግብር ከፋይ መረጃ፣ ታክስን በትክከል አስታውቆ በመክፈል፣ በቅጣት ታሪክ፣ በኦዲት ግኝት እና በግብር ስሌት እንዲሁም በተመላሽ ጥያቄ ልዩነት፣ በወጪና ገቢ ንግድ በታየ የሕግ ተገዥነት፣ በእዳ አከፋፈል ታሪክ እና በታክስ ማጭበርበርና ስወራ መስፈርቶች ታይተው ነው።

# Excise

Continued from page 7

caused several difficulties in the early life of the new organization. Many of the monitoring and inspection functions, and corresponding powers, were later split off to form a new UK Border Agency, while the residual organization is now merely responsible for the financial aspects of collection.

***United States***

In the United States, the term "excise" has at least two meanings: (A) any tax other than a property tax or capitation (i.e., an excise is an indirect tax in the constitutional law sense), or (B) a tax that is simply called an excise in the language of the statute imposing that tax (an excise in the statutory law sense, sometimes called a "miscellaneous excise"). An excise under definition (A) is not necessarily the same as an excise under definition (B).

An excise (under definition B) has been defined as '"a tax upon manufacture, sale or for a business license or charter, as distinguished from a tax on real property, income or estates."

Both the federal and state governments levy excise taxes on goods such as alcohol, motor fuel, and tobacco products. The laws of the federal government and of some state governments impose excises known as the income tax. Even though federal excise taxes are geographically uniform, state excise taxes vary considerably. Taxation constitutes a substantial proportion of the retail prices on alcohol and tobacco products.

Local governments may also impose an excise tax. For example, the city of Anchorage, Alaska charges a cigarette tax of $1.30 per pack, which is on top of the federal excise tax and the state excise tax. In 2011, the United States federal excise tax on gasoline was 18.4 cents per gallon (4.86 ¢/L) and 24.4 cents per gallon (6.45 ¢/L) for diesel fuel.

***Ethiopia***

Excise tax in Ethiopia is imposed and payable on selected goods, such as, luxury goods and basic goods which are demand inelastic. Moreover, it is believed that imposing the tax on goods that are hazardous to health and which are cause to social problem (such as alcohol and cigarette) will reduce the consumption of such goods.

Recently, the government believes and made change or amendment on this tax, but it's on process to be approved by the house of people's representatives, the Ethiopian revenue ministry and ministry of finance together where the responsible organizations to prepare the amendment and bring to discussion with different stockholders before send to the house of peoples representatives for the approval, in the new amendment many basic goods set free from the tax, on the contrary some goods like a used car that causes air pollution and car accidents in the country charges more excise tax rate, and its believed that the tax will approved and put into practice soon.

Source: - Wikipedia and other websites

# ከሲንጋፖር እንማር

ከገጽ 8 የዞረ

አምስት ሰዎች ከብራዚል ተነስተው በእጅ በሚያዙ ሻንጣዎችና ቦርሳዎች፤ በድምሩ 47.4 ኪሎ ግራም ኮኬይን በቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ በኩል ወደተለያዩ ሀገራት ለማዘዋወር ሲሞክሩ ከአደንዛዥ ዕፁ ጋር ህዳር 5/2012 ዓ.ም. ተይዘዋል፡፡ የአደንዛዥ ዕፅ አዘዋዋሪዎቹ መዳረሻ የታይላንዷ ከተማ ባንኮክ እና የሩዋንዳዋ ኪጋሊ ነበሩ፡፡

በሀገር ውስጥ ሲዘዋወሩ ከተደረሰባቸው አደንዛዥ ዕፆች መካከል በአንድ ሳምንት ውስጥ ሞያሌ አካባቢ የተያዘው 2ሺ 720 ኪሎ ግራም ሀሺሽ ይገኝበታል፡፡ ጥር 25/2011 ዓ.ም. በአንድ ቀን ብቻ ያቤሎ የመቆጣጠሪያ ላይ 1ሺ 971 ኪሎ ግራም የሚመዝን አደንዛዥ ዕፅ ተይዟል፡፡ የተያዘው መጠን በጣም አስደንጋጭ ቢሆንም ያልተደረሰበት ሊኖር እንዲሚችል ይገመታል፡፡ ያደጉ አገራት የችግሩን አሳሳቢነት በመረዳታቸው በኩንታል የሚገለፅ መጠን ይቅርና የልብስ አዝራር የሚያህል መጠን ሲያገኙ የሚሰጡት ግምትና የሚሰሩት ኦፕሬሽን ያስገርማል፡፡ አነፍናፊ ውሻ በመጠቀም ክትትል እና ፍተሻ ያደርጋሉ፡፡ ወንጀለኞች ላይ የሚወስዱት እርምጃም ቀላል አይደለም፡፡

እንደ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጥናት ከሆነ ችግሩ በሀገራችንም እየሰፋ እንደሆነ ያሳያል፡፡ የመንግሥታቱ ድርጅት ይፋ ባደረገው የጥናት ውጤት ኢትዮጵያ እጅግ አሳሳቢ በሆነ ሁኔታ አደገኛ እፅ ተጠቃሚዎች ያሉባት ሀገር እንደሆነች ይፋ አድርጓል፡፡

በሀገራችን የጎዳና ተዳዳሪዎች የአደንዛዥ ዕፅ ዋና ተጠቃሚዎች ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ ከዚህ ባለፈ የሀገራችን ሚዲያዎች በሚሠሯቸው ዘገባዎች ዕውቀት የሚገበይባቸው እና መልካም ሥነ-ምግባር የተላበሰ ዜጋ ለመፍጠር ጥረት የሚደረጉባቸው ትምህርት ቤቶች ሳይቀሩ የአደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚዎች እንዳሉ ይጠቁማሉ፡፡ ችግሩን በጣም አሳሳቢ የሚያደርገው ለታዳጊዎች በድብቅ ከልዩ ልዩ ምግቦች ጋር ደባልቆ በመስጠት በሱስ እንዲጠመዱ የማድረግ እንቅስቃሴ መኖሩ ነው፡፡ ይህ እንቅስቃሴ በእጅጉ ሊያሳስበን ይገባል፡፡ ቆም ብለን ችግሩን በምን መንገድ መፍታት እንዳለብን ካልመከርን እየቆየ ከቁጥጥራችን ውጪ መሆኑ የማይቀር ነው፡፡

ሀገራት እንደ ሁኔታው የሚለያይ የአደንዛዥ ዕፅን ለመቆጣጠር እስከ ሞት የሚያስቀጣ ሕግ አውጥተዋል፡፡ የሕግ ማዕቀፍ ከማውጣት በተጨማሪ ትውልድን ማስተማር ላይ ትኩረት አድርገው የሚሠሩ ሀገራት አሉ፡፡ ለአብነት ሲንጋፖርን ማየት የሚቻል ሲሆን ሀገራችን ከሲንጋፖር ወስዳ ልትተገብራቸው የምትችላቸው ጥሩ ልምዶች አሉ፡፡



ሲንጋፖር ጠበቅ ያለ የፀረ-አደንዛዥ ዕፅ ፖሊሲ አላት፡፡ የሲንጋፖር ተሞክሮ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውስጥ በተሞክሮነት ቀርቦ ነበር፡፡ የሲንጋፖር አደንዛዥ ዕፅ ቁጥጥር ለየት የሚያደርገው ህፃናት ሲያድጉ አደንዛዥ ዕፅ ውስጥ እንዳይገቡ ቀድመው የሚከላከሉበት እና በሥነ-ምግባር አንፀው የሚያሳድጉበት መንገድ ነው፡፡ በቀላል መንገድና አቀራረብ ለልጆች በተረት መጽሐፍ ቀርቦላቸው በሥርዓተ-ትምህርት ውስጥ ተካትቶ እንዲማሩ ይደረጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ወላጆች ልጆቻቸውን እንዴት ከአደንዛዥ ዕፅ መከላከል እንዳለባቸው የሚያስገነዝብ መጽሐፍ (ሃንድ ቡክ) ተዘጋጅቶ ይቀርብላቸዋል፡፡

በተረት መልክ የዐይጥ፣ የድመት፣ የጥንቸልና የካንጋሮ ገጸ ባህሪ በመውሰድ ልጆቻቸውን በቀላሉ በስነ-ምግባር ታንፀው እንዲያድጉ ቤተሰብም ሆነ ትምህርት ቤት የድርሻውን ይወጣል፡፡

ከቤተሰብ ጀምሮ ከተሠራ ህፃናት ሲያድጉ ከአደንዛዥ ዕፅ ነፃ የሆነ ህይወት እንዲመሩ ያግዛቸዋል፡፡ ካደጉ በኋላ በአቻ ግፊት በቀላሉ ወደ ዕፅ እንዳይገቡ ጠንካራ አስተሳሰብ እንዲኖራቸው እና መንፈሰ ጠንካራ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል፡፡

በሀገራችን፤ ስለኮንትሮባንድ አስከፊነትና በኮንትሮባንድ ውስጥ ደግሞ ስለአደንዛዥ ዕፅ ጎጂነት የሲንጋፖርን ያህል ባይሆንም በመጠኑ በየት/ቤቱ መልዕክቶች ሲተላለፉ፤ በሥነ-ምግባርና ሥነ-ዜጋ ትምህርት ውስጥም ጠቀስ ተደርጎ ግንዛቤ ሲሰጥ ይታያል፡፡ ሆኖም ግን፤ እየታየ ካለው የዕፁ ተጠቃሚነት እየበዛ ከመምጣት አንጻር እንቅስቃሴው ተመጣጣኝ አይደለም፡፡

በሌላ በኩል ግን ኮንትሮባንድ በህዝብ ደህንነት፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገቶች ላይ የሚያስከትለው ተፅዕኖ በርካታ በመሆኑ ይህን ለመከላከል የወጡ የጉምሩክ ሕጎች የአደንዛዥ ዕፅ ዝውውርን ለመቆጣጠርም የሚወሰዱ እርምጃዎችን እንዲያካትቱ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት፤ የጉምሩክ ሕግን መጣስ አስተዳደራዊና የወንጀል ቅጣት የሚያስከትል ሲሆን ተፈጽሞ ሲገኝ እስከ ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ) እና እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ያስቀጣል፡፡

ሕጉን ተግባራዊ ለማድረግ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የጉምሩክ ኬላዎች እና መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ተቋቁመው ሌት ተቀን የቁጥጥር ሥራዎች የሚከናወኑበት የአሠራር ሥርዓቶች ተዘርግተዋል፡፡ በየብስና በአየር ተጓጉዘው የሚገቡ ዕቃዎች በሕዝብ ደህንነትና ሰላም ላይ አደጋ እንዳይጥሉ በመግቢያና መውጫ በሮች ላይ በማሽን የታገዘ ፍተሻ ይከናወናል፡፡ በእርግጥ የቁጥጥር ሥራው ከችግሩ አሳሳቢነት አንፃር ከዚህ በላይ በቴክኖሎጂ የተደገፈ አሠራር ተግባራዊ ማድረግን የሚጠይቅ ነው፡፡ በሚደረጉ ፍተሻዎች አደንዛዥ ዕፅን ጨምሮ ሌሎች ወደ ሀገር እንዳይገቡ የተከለከሉ ጎጂ ምርቶች በሕገ-ወጦች መንገድ ደብቀው ወደ ሀገር ለማስገባት ጥረት ሲያደርጉ ተደርሶባቸዋል፡፡ እነዚህ ሕገ-ወጦች በሚያጓጉዟቸው ዕቃዎች የሚደርሰውን አደጋ ተገንዝበው ዕቃዎቹ ወደ ሀገር ገብተው ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ሲታገሉና ሲተጉ እስከ ሕይወት መስዋዕትነት ጭምር የሚከፍሉ የጉምሩክ ሠራተኞች አሉ፡፡ በቅርቡ እንኳን በሥራ ላይ እያሉ ህይወታቸውን ያጡ የሞያሌ እና የባህርዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሠራተኞችን ማስታወስ በቂ ነው፡፡

ሌላው የአደገኛ ዕፅ ዝውውርን ለመከላከል ከጉምሩክ ሕጎች በተጨማሪ ሌሎች ሕጎች እና ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተግባራዊ ለማድረግ የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ ነው፡፡ እነዚህ የሕግ ማዕቀፎችና የሕግ ማዕቀፎቹን ተግባራዊ ለማድረግ የሚሠሩ ሥራዎች በተቆጣጣሪ መሥሪያ ቤቶች ጥረት ብቻ ችግሩን መግታት አይቻልም፡፡ በተለይም የአደገኛ ዕፅ ዝውውር በባህሪዩ ውስብስበና በቀላሉ እንዳይደረስበት በየጊዜው የማታለያ ዘዴዎችን በመጠቀም የሚከናወን ስለሆነ የማታለያ ዘዴዎቹን እየተከታተሉ የማስወገድ ስልቶች እየተሠራባቸው ነው፡፡

በመሆኑም ሁሉም ዜጋ የአደገኛ ዕፅ አዘዋዋሪዎችን ሲመለከቱ ባለመታገስ፣ በጉዞ ወቅት የማያውቁትን መንገደኛ በግልፅ የማይታወቅ ዕቃ ለማጓጓዝ ባለመተባበር እና ጥቆማ በመስጠት ተሳትፎውን ማጠናከር አለበት፡፡ ከሁሉም በፊት ግን የትምህርት ተቋማት፣ መገናኛ ብዙኃን እና የተለያዩ ተቋማት የማስተማር እና የመከላከያ ግንዛቤዎችን መሥራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

# ስእንግዶቹ ፈጣን...

ከገጽ 1 የዞረ

ከአሜሪካ ኮሎምበስ ግዛት የመጡት ወይዘሮ ውበት በላቸው እና ወ/ሮ አጋር ወልዴ፤ መልካም አቀባበልና ፈጣን የጉምሩክ አገልግሎት ማግኘታቸውን ገልፀው በቆይታቸው የተለያዩ የኢንቨስትመንት አማራጮችን በማጤን እና ኢንቨስት በማድረግ ሰፊ የሥራ እድልን ለመፍጠር እንዲሁም ምርቶችን ወደ ውጭ ሀገራት በመላክ ሀገራችን በቂ የውጭ ምንዛሪ እንድታገኝ እንደሚሠሩም ጠቁመዋል፡፡

# Tips

BY TSETARGACHEW NIGATU

# Excise Tax




*Excise* is derived from the Dutch *accijns*, which is presumed to come from the Latin *accensare*, meaning simply "to tax".

Excise was introduced in the mid-17th century under the Puritan regime. In the British Isles, upon the Restoration of the Monarchy, many of the Puritan social restrictions were overturned, but excise was re-introduced, under the Tenures Abolition Act 1660, in lieu of rent, for tenancies of royally-owned land which had not already become socage. Although the affected tenancies were limited in number, the excise was levied more generally; at the time, there was thought to be a rough correspondence between the wealthy manufacturers of affected goods, and the wealthy tenants of royal land.

Excise duties or taxes continued to serve political as well as financial ends. Public safety and health, public morals, environmental protection, and national defense are all rationales for the imposition of an excise. In defense of excises on strong drink, Adam Smith wrote: "It has for some time past been the policy of Great Britain to discourage the consumption of spirituous liquors, on account of their supposed tendency to ruin the health and to corrupt the morals of the common people."

As a deterrent, excise is typically directed towards three broad categories of harm:

- health risks from abusing toxic substances (thus making it a kind of sumptuary tax); typically this includes tobacco and alcohol
- environmental damage (thus acting as a green tax); this usually includes fossil fuels (such as petrol)
- socially damaging / morally objectionable activity (thus making it a type of vice tax or sin tax); usually this includes gambling, and can include prostitution (including solicitation and pimping) in places where it is legal

Monies raised through excise may be earmarked for redress of specific social costs commonly associated with the product or service on which it is levied. Tobacco tax revenues, for example, might be spent on government anti-smoking campaigns, or healthcare for cancer, heart disease, vascular disease, lung disease, and so on.

In some countries, excise is also levied on some goods for purely punitive reasons. Many US states impose excise on illegal substances; these places do not consider it to be a revenue source, but instead regard it as a means of imposing a greater level of punishment, by opening up convicted criminals to the charge of tax evasion

***Targets of taxation***

***Tobacco, alcohol and gasoline***

These are the three main targets of excise taxation in most countries around the world. They are everyday items of mass usage (even, arguably, "necessity") which bring significant revenue for governments. The first two are considered to be legal drugs, which are a cause of many illnesses (e.g. lung cancer, cirrhosis of the liver), which are used by large swathes of the population, both being widely recognized as addictive. Gasoline (or petrol), as well as diesel and certain other fuels, meanwhile, have excise tax imposed on them mainly because they pollute the environment and to raise funds to support the transportation infrastructure

***Around the world***

***Australia***

The Australian Taxation Office describes an excise as "a tax levied on certain types of goods produced or manufactured in Australia. These... include alcohol, tobacco and petroleum and alternative fuels".

In Australia, the meaning of "excise" is not merely academic, but has been the subject of numerous court cases. The High Court of Australia has repeatedly held that a tax can be an "excise" regardless of whether the taxed goods are of domestic or foreign origin; most recently, in *Ha v New South Wales* (1997), the majority of the Court endorsed the view that an excise is "an inland tax on a step in production, manufacture, sale or distribution of goods", and took a wide view of the kind of "step" which, if subject to a tax, would make the tax an excise.

***Canada***

Both the federal and provincial governments impose excise taxes on inelastic goods such as cigarettes, gasoline, alcohol, and for vehicle air conditioners. A great bulk of the retail price of cigarettes and alcohol are excise taxes. The vehicle air conditioner tax is currently set at $100 per air conditioning unit. Canada has some of the highest rates of taxes on cigarettes and alcohol in the world. These are sometimes referred to as sin taxes.

***India***

In India, almost all products are subject to excise duty, provided the following four conditions are fulfilled:

- There should be a manufacture
- The manufacture was in India (excluding special economic zone)
- The manufacture should result in goods
- The goods thus manufactured must be excisable (means the goods must be specified in central excise tariff act,1985)

In India, the Government has produced an automatic centralized system for paying excise. With this, manufacturers can easily pay their excise online on every 5th of the following month through GAR-7/ Performa for Service Tax Payments/

***United Kingdom***

In the United Kingdom, the following forms of excise are levied on goods and services:

- Air Passenger Duty (Finance Act 1994)
- Aggregates Levy (Finance Act 2001)
- Alcohol duties (Beer Duty, Wine Duty, Cider Duty, Spirits Duty) (Alcoholic Liquor Duties Act 1979)
- Bingo Duty (Betting and Gaming Duties Act 1981)
- Climate Change Levy (Finance Act 2000)
- Gambling duties (General Betting Duty, Pool Betting Duty, Remote Gaming Duty) (Finance Act 2014)
- HGV Road User Levy (HGV Road User Levy Act 2013)
- Hydrocarbon Oil Duty (Hydrocarbon Oil Duties Act 1979)
- Landfill tax (Finance Act 1996)
- Machine Games Duty (Finance Act 2012) (formerly Amusement Machine License Duty)
- Tobacco Duty (Tobacco Products Duty Act 1979)
- Vehicle Excise Duty (Vehicle Excise and Registration Act 1994)

Historically, these were collected by the *Board of Excise*, which was subsequently combined with the Inland Revenue (responsible for collecting direct taxes). In view of the higher likelihood of organized crime being involved in attempts at evading Excise, and its association with smuggling, compared with evasion attempts concerning direct taxation, the *Board of Excise* was later combined instead with the *Board of Customs*, to form HM Customs and Excise. In this combined form, *Customs and Excise* was responsible for managing the import and export of goods and services into the UK, and its officers wielded greater powers of access, arrest, and seizure, than the Police.

On 18 April 2005, *Customs and Excise* was merged once more with the Inland Revenue to form a new department, HM Revenue and Customs (*HMRC*). The enormous contrast between the powers of officers of the Inland Revenue, and those of *Customs and Excise*, initially

Continued on page 6

# ሕገ-ግብር

አዘጋጅ- ሰዒድ ገልገሉ

ይህ አምድ የታክስ አስተዳደርና የጉምሩክ አሠራር የሚመራበትን ህጐች፣ መመሪያዎችና አሰራሮች፣ ለሕግ ተገዢነት የሚያስተምሩ አስተሳሰቦችን፣ ሕጎችን ለአሠራር ምቹ የሚያደርጉና ፍትሃዊ የንግድ ውድድርን የሚያጎለብቱ አሰራሮችንና ተሞክሮዎችን የሚያስተዋውቅ ጽሑፍ ይቀርብበታል፡





## የኬላዎቻችን ቅኝት

ኮንትሮባንድ፤ በተለይም እንደኛ እምቅ አቅምና ሀብት ባላቸው ታዳጊ ሀገራት ለማደግ የሚደረገውን ትግል ሲያስተጓጉል መመልከት የተለመደ ነው። በርካታ ቢሊየን ብር የሚያስገኙ የሀገር ሀብቶች እንደዋዛ ከግዛታችን ይወጣሉ፤ የሌሎች ሀገራት ሲሳይም ይሆናሉ። ተገቢውን ቀረጥና ታክስ ለመንግሥት እና ለህዝብ ሊያስገኙ የሚችሉ የተለያዩ ሸቀጣ ሸቀጦች የተለያዩ ማሳለፊያና ማታለያ መንገዶችን በመጠቀም በስውር ይገባሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ይሄንኑ ሕገ-ወጥነት ለመፋለም የሚደረጉ ጥረቶች የአካልና የሕይወት መስዋዕትነትን በከፍተኛ ደረጃ የጠየቁ መሆናቸው ነው።

በሀገራችን የኮንትሮባንድ መከላከል ሥራው እስከነክፍተቱም ቢሆን ውጤቶችን እያሳየ የመጣበት ጊዜ መሆኑን እናያለን። በተለይም ባለፉት ሦስትና አራት ዓመታት በኮንትሮባንድ ዋነኛ መግቢያና መውጫ ቦታዎች ላይ አስፈላጊውን የቁጥጥር ሥራ በማጠናከር በርከት ያሉ ሥራዎች ተሠርተዋል። በሳለፍነው 2013 የበጀት ዓመት ብቻ ከ3.6 ቢሊየን ብር በላይ ዋጋ ያላቸው የተለያዩ የገቢና የወጪ ኮንትሮባንድ ዕቃዎችን ለመያዝ ተችሏል።

ለሥራ በተዘዋወርንባቸው አንዳንድ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች የተሻለ የሥራ አፈጻጸም መኖሩን ተመልክተናል። ሕጎች ተጥሰው ሲገኙ የሕግ አስከባሪ ግብረ-ኃይሉ በተቀናጀ መልኩ ከፀጥታ ኃይሎችና ከደኅንነት አካላት ጋር ርብርብ እያደረጉ መሆኑን ታዝበናል። የኮንትሮባንድ መከላከል ሠራው የመንግሥት ዋነኛ የትኩረት መስክ ተደርጎ በመወሰዱ የሚገኙ ውጤቶችም ይሄንኑ የሚገልፁ ናቸው። ከተሠሩ የማሻሻያ ሥራዎች መካከልም በተቋቋሙበት ቦታ ሳቢያ ውጤታማነታቸው እምብዛም የነበሩ ኬላዎች እንዲነሱ መደረጋቸው፣ የኮንትሮባንድ ማነቂያ (ዋነኛ የሆነውን ይህን የኮንትሮባንድ መተላለፊያ ቁልፍ መቆጣጠሪያ) ቦታዎች ሆነው ሳለ ቀድሞ በነበረው የአመራር ክፍተት ለኬላነት ያልተመረጡ ቦታዎችን ኬላ እንዲመሰረትባው በማድረግ አመርቂ ሥራዎች ተሠርተዋል። በዚህም በርካታ ተጨማሪ ኬላዎች ወሳኝ በሆኑ ቦታዎች ላይ እንዲተከሉ ተደርጓል።

የሥራ ቅኝት ካደረግንባቸው ኬላዎች አንዱ በሀዋሳ ጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤት ስር የሚገኘው የኮንሶ ኬላ ነው። የኮንሶ ኬላ ከሞያሌ መነሻቸውን አድርገው በያቤሎ አርባምንጭ ሃዋሳ እና ሌሎች አካባቢዎች መዳረሻቸውን የሚያደርጉ ተሽከርካሪዎች የሚመላለሱበት መስመር ነው። ቦታው «የኮንትሮባንድ ዋነኛ መተላለፊያ» ተብለው ከተለዩ ቦታዎች መካከል አንዱ ሲሆን በተደጋጋሚ የተለያዩ የገቢና ወጪ የኮንትሮባንድ ዕቃዎች ይያዙበታል። የአካባቢው መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ሥራውን አስቸጋሪ የሚያደርገው ቢሆንም የሀገርን አደራ ለተሸከሙት የጉምሩክ ፈታሽ ባለሙያዎችና ለፌደራል ፖሊስ አባላት ግን ምናቸውም አይደለም። በዚህ ኬላ የኮንትሮባንድ ፍሰቱ የሚካሄደው በግራና በቀኝ ባሉ ቀጫጭን የጫካ መንገዶችም ጭምር ነው። ይህንንም ለመከላከል የፌደራል ፖሊስ አባላት ሳይሰለቹ ብዙ ርቀቶችን በእግራቸው በመጓዝ (በደፈጣ) የቁጥጥር ሥራቸውን ያከናውናሉ።

ሌላው የቃኘነው ኬላ የጪጩ መቆጣጠሪያ ጣቢያ ነው። ኬላው በተመሳሳይ በሃዋሳ ጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤት ስር የሚገኝና በዲላ ከተማ መውጫ ላይ የቆመ ነው። በዚህ ኬላ ተሽከርካሪዎች ከመሀል ሀገርና ከሌሎች ከተሞች ወደ ያቤሎ እና ሞያሌ የሚመላለሱበት መስመር ነው። የተለያዩ አልባሳት፣ ጫማዎችና የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ከሚያዙበት ገቢ የኮንትሮባንድ ዕቃዎች መካከል ናቸው። የቀንድ ከብቶች እና ሌሎች ማዕድናት ደግሞ በወጪ ኮንትሮባንድ የሚያዙ ናቸው። መነሻቸውን ከሻሸመኔ ከተማና ከሌሎች ቦታዎች ያደረጉ አደንዛዥ ዕፆችም ወደ ኬንያ ሊያልፉ ሲሉ በዚህ ኬላ በተደጋጋሚ በቁጥጥር ስር ይውላሉ። ቦታው ከተማ አቅራቢያ እንደመሆኑ የፍተሻ ሥራውን ፈታኝና ቅልጥፍናን ከጥንቃቄ ጋር የሚጠይቅ ነው።

የኮንትሮባንድ መከላከል ሥራው ካለፉት ጊዜያት አንፃር እመርታ የታየበት ቢሆንም አሁንም ሊቀረፉ የሚገባቸው ጉዳዮችም አሉ። አንደኛው የአሠራር ማሻሻያ ነው። የፍተሻ ሥራዎች ወቅቱ በሚጠይቀው ቴክኖሎጂ የታገዙ መሆን ይኖርባቸዋል። በእርግጥ እንደ ጋላፊና አዋሽ በመሳሰሉ ኬላዎች ላይ የስካኒንግ ማሽን (Scanning machine) የፍተሻ ሥራውን በእጅጉ እያገዘው መሆኑን ተመልክተናል። ከላይ በተጠቀሱት ኬላዎችም ይህ አሠራር ሊሰፋ ይገባዋል። በሌላ በኩል ለፍተሻ ሥራው የሚያመች ቦታ እጥረት መኖሩን ታዝበናል። ፈተሻው የሚከናወነው የተሽከርካሪ መንገድ ላይ በመሆኑ ለከተማ በቀረቡ እንጪጩን በመሰሉ ኬላዎች ከፍተኛ የትራፊክ መጨናነቅን የሚፈጥር ነው።

የኮንትሮባንድ መከላከል ሥራው ከኅብረተሰቡ ተሳትፎ ውጪ በፍፁም ውጤታማ ሊሆን አይችልም። ተዘዋውሬ በተመለከትኳቸው ኬላዎች የተሠሩ ሥራዎች መልካም ቢሆኑም የኅብረተሰቡ ተሳትፎ ግን በሚፈለገው ልክ አለመሆኑን ታዝቤያለሁ። በተለያዩ መንገዶች ለኮንትሮባንዲስቶች መረጃ መስጠት፣ የኮንትሮባንድ ዕቃዎችን በመኖሪያ ቤት መደበቅ እና ተባባሪ ሆኖ በሸክም ለማሳለፍ መሞከር በአንዳንድ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ያስተዋልኩትና የሰማሁት ሀቅ ነው። በኮንትሮባንድ ንግድ የተነሳ ኑሮው የሚናጋውና ሰላሙንና ጤናውን የሚያጣው እራሱ ማህበረሰቡ ስለሆነ ኮንትሮባንድ ላይ የሚደረገውን ትግል መደገፍና መተባበር ማኅበራዊ ግዴታው ነው። የኮንትሮባንድ አስከፊነትን ለመረዳት የሚያዙ የጦር መሳሪያዎች፣ ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድሃኒቶችና አደንዛዥ ዕፆችን ማየት ብቻ በቂ ነው። ሀገር የምትድነው አንድ ዓላማ ይዘን ስንታገል ነውና በነዚህና በሌሎች ምክንያቶች ዜጎች ከሚጎዱና ኢኮኖሚያችን ላይ ከሚፈጥር ይህ አይነት ተግባር መገታት ይኖርበታል። ለዚህ ደግሞ ሁሉን አቀፍ ተሳትፎ ወሳኝነቱ የጎላ ነው።

## ከሲንጋፖር እንማር

**ከጋሻው ታደሰ**

አደንዛዥ ዕፅ ከጤና ጠንቅነት የዘለለ መዘዝ አለው። የዜጎችን ተስፋ እና ህልም በመንጠቅ ለውድቀት መንገድ ያመቻቻል። በተለይም ወጣቶችን ከትምህርት ገበታቸው እና ከሥራቸው በማፈናቀል ተወዳዳሪ የለውም። አምራችነትን በመጉዳት እና የማህበረሰብ እሴትን በመሸርሸር በአገር ላይ ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ቀውስ ያስከትላል።

የአደንዛዥ ዕፅ ዝውውሩ እየሰፋ ከሄደ በህገወጥ ንግድ በሚገኘው ገቢ ዕጽ አዘዋዋሪዎቹ ኔትወርክ ፈጥረው የጸጥታ አካላትን የሚገዳደር አደገኛ የማፊያዎች ቡድን ይፈጥራል። የማፊያ ቡድኖች ሲፈጠሩ የዜጎች ሰላማዊ እንቅስቃሴ ይስተጓጎላል፣ ሰብአዊ መብቶች ይጣሳሉ። ሜክሲኮ አካባቢ የሚስተዋለው ግድያ፣ የሴቶች መደፈር እና ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ከአደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚነት ምክንያትም ጋር የሚያያዝ ነው።

በሀገራችንም የአደገኛ ዕፅ አዘዋዋሪዎች እና ተጠቃሚዎች እንዳሉ ማሳያ የሚሆኑ ልዩ ልዩ ዕጾች በገፍ ከሀገር ሲወጡና ወደ ሀገር ሲገቡ በጉምሩክ ኬላዎች እየተያዙ ነው።

ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት ካልተዘረጋ እና ርብርብ ካልተደረገ የአደንዛዥ ዕፅ አዘዋዋሪዎች ኢትዮጵያን ዋነኛ መሸጋገሪያ ማድረጋቸው የማይቀር ነው። በቦሌ አርፖርት በተለያየ ጊዜ የተያዙት አደገኛ አደንዛዥ ዕፆች ይህንን ሀሳብ የሚያጠናክሩ ናቸው። ቀደም ሲል የጉምሩክ ኮሚሽን ካወጣቸው ሪፖርቶች መካከል አንድ ናይጄሪያዊ ዜጋ በያዘው ቀላል ሻንጣ ውስጥ 10.8 ኪሎ ግራም ሔሮይን እና ኮኬይን የተባሉ አደንዛዥ እፆችን ደብቆ ለማለፍ ሲሞክር ተይዟል። እንዲሁም አንዲት የደቡብ አፍሪካ ዜጋ ከደቡብ አፍሪካ ተነስታ ወደ ህንድ ደልሂ ለመጓዝ ስትሞክር ይዛ የተገኘችው 7.4 ኪግ ኮኬይን ነው። የአዘርባጃን ዜጋ የሆነች ሴት ከሞስኮ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ሆቴል አርፋ ተመልሳ ወደ ባንኮክ ልትወጣ ስትል ከያዘችው አራት ኪሎ ግራም ኮኬይን ጋር በቁጥጥር ሰር ውላለች። የጉዞ መዳረሻው ህንድ የነበረ አሜሪካዊ በሻንጣው ውስጥ ሻግ በመስራት 5.2 ኪሎ ግራም ኮኬይን እንደያዘ በቁጥጥር ስር ውሏል።

ወደ ገጽ 6 ዞሯል



### የገቢዎች ሚኒስቴር ራዕይ

በ2022 ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ተገንብቶ ሀገራዊ ወጪ በታክስ ገቢ ተሸፍኖ ማየት

### እ ሴ ቶ ች

1. አገልጋይነት (Customer centric)
2. ሙያዊ ብቃት (Professionalism)
3. በቡድን መሥራት (Team work)
4. መሰጠት (Dedication/commitment)
5. ታማኝነት (Loyality)